የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፩ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.1
ADDIS ABABA, 28th October, 2024

## ማውጫ

የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፭፻፶፱/ ፪ሺ፲፯ ……ገጽ ፲፯ሺ፫፻፯

## ደንብ ቁጥር ፭፻፶፱ /፪ሺ፲፯

**<u>የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬ / ፩ሺ፱፻፺፯ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፩ሺ፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ ደንብ "የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፭፻፶፱/ ፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>ማሻሻያ</u>**

የኢሚግሬሽን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፬/፩ሺ፱፻፺፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የደንቡ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፫) እና (፭) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፭) ተተክቷል፡-

"፫/ **"አገልግሎት"** ማለት የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ነው፤

፭/ **"አዋጅ"** ማለት የኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፬/፩ሺ፱፻፺፭ ( እንደተሸሻሻለ) ነው፡፡"

## Content

Council of Ministers Immigration Amendment Regulation No 559/2024. ……….Page17307

## REGULATION NO. 559/2024

**<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMENDMENT FOR IMMIGRATION REGULATION NO. 114/2005</u>**

This Regulation is issued by the Federal Democratic Republic of Council of Ministers pursuant to Sub Article (1) of Article 23 of the Immigration Proclamation No.354/2003 (as amended).

**1. <u>Short Title</u>**

This Regulation may be cited as the "Council of Ministers Immigration amendment Regulation No. 559 / 2024".

**2. <u>Amendment</u>**

Immigration Council of Ministers Regulation No. 114/2004 is hereby amended as follows:

1/ Article 2(3) and 5 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub-Article 3 and 5 :

"3/ **"Service"** means the Immigration and Citizenship Service;

5/ **"Proclamation"** means Immigration Proclamation No. 354/2003 (as amended). "

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ) እና (ሐ) ተሰርዘው እንደ ቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ተተክተዋል፡-

"ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት፡-

(፩) ዕድሜያቸው እስከ ፳፭ ዓመት ለሆኑ ሰዎች የፓስፖርት አገልግሎት ጊዜ ………….... አምስት ዓመት፤

(፪) ዕድሜያቸው ከ ፳፭ ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች የፓስፖርት አገልግሎት ጊዜ …………… አሥር ዓመት፡፡

ለ) ሰርቪስ ፓስፖርት፡-

(፩) ዕድሜያቸው እስከ ፳፭ ዓመት ለሆኑ ሰዎች የፓስፖርት አገልግሎት ጊዜ ………….... አምስት ዓመት፤

(፪) ዕድሜያቸው ከ ፳፭ ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች የፓስፖርት አገልግሎት ጊዜ ……… አሥር ዓመት፡፡

ሐ) መደበኛ ፓስፖርት፡-

(፩) ዕድሜያቸው እስከ ፳፭ ዓመት ለሆኑ ሰዎች የፓስፖርት አገልግሎት ጊዜ ………….... አምስት ዓመት፤

(፪) ዕድሜያቸው ከ፳፭ ዓመት በላይ የሆኑ ሰዎች የፓስፖርት አገልግሎት ጊዜ …………… አሥር ዓመት፡፡"

፫/ የደንቡ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ የስራ ቪዛ በሚከተሉት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ለሚመጡ የውጭ ሀገር ሰዎች ይሰጣል፡-

ሀ) ለኢንቨስትመንት፤

ለ) ለመንግስታዊ ስራዎች፤

ሐ) ለሀገር ውስጥ ወይም ለውጭ ባለሀብት ተቀጣሪ፤

መ) መንግስታዊ ላልሆነ ድርጅት ሰራተኞች፤

2/ Paragraph (a), (b) and (c), of Sub-Article (1) of Article 11 of the Regulation are deleted and replaced by the following new paragraph (a), (b) and (c) respectively:

" a) Diplomatic passport:

(1) Passport service period for persons up to 25 years of age............... Five years;

(2) Passport validity period of persons over 25 years of age ............... Ten years.

b) Service Passport:

(1) Passport service period for persons up to 25 years of age ............... Five years;

(2) Passports validity period of persons over 25 years of age ......... Ten years.

c) Ordinary Passport:

(1) Passport service period for persons up to 25 years of age ............... Five years;

(2) Passport validity period of person over 25 years of age ............... Ten years. "

3/ Sub-Article (1) of Article 16 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1):

"1/ Business visas are issued to foreign persons coming to Ethiopia for the following reasons:

a) for investment;

b) for government operations;

c) an employee of a domestic or foreign investor;

d) employees of a non-governmental organization;

ሠ) ለስልጠና፤

ረ) ለሚዲያ ስራ፤

ሰ) ለንግድ እና ገበያ ጥናት፤

ሸ)ለመዝናኛ ኢንዱስትሪ፤ወይም

ቀ) ለስፖርት ውድድር ወይም ልምምድ፡፡”

፬/ ከደንቡ አንቀጽ ፳ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፳፩፣ ፳፪ እና ፳፫ ተጨምረው ነባሮቹ አንቀጽ ፳፩ - ፵፩ የነበሩ አንቀጾች ከአንቀጽ ፳፬- ፵፬ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

“፳፩. <u>የህክምና ቪዛ</u>

የህክምና ቪዛ የሚሰጠው ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ በዘመናዊ፣ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ መንገድ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ወይም ለማግኘት ለሚፈልግ እና ህጋዊና ግዜው ያላለፈበት የጉዞ ሰነድ ለሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

፳፪. <u>ኃይማኖታዊ ቪዛ</u>

ኃይማኖታዊ ቪዛ የሚሰጠው ለኃይማኖታዊ ጉዳይ ብቻ ወደ ሀገር ዉስጥ እንዲገባ ለተጋበዘ ወይም ለተጠየቀለት እና ህጋዊ የጉዞ ሰነድ ለሚያቀርብ ሰው ነው፡፡

፳፫. <u>የቤተሰብ ወይም የእጮኛ ቪዛ</u>

የቤተሰብ ወይም የእጮኛ ቪዛ የሚሰጠዉ ቤተሰብ ለመጠየቅ ወይም እጮኛዉን ለማግኘት ለሚያመለክት እና ህጋዊና ግዜው ያላለፈበት የጉዞ ሰነድ ለሚያቀርብ ሰው ነዉ፡፡ ”

፭/ ከደንቡ አንቀጽ ፴፰ (በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀፅ (፬) ላይ እንደተሸጋሸገው) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ክፍል “ክፍል ስምንት” እና አንቀጽ ፴፱፣፵ እና ፵፩ የተጨመረ ሲሆን ነባሩ ክፍል ስምንት ክፍል ዘጠኝ ሆኖ ነባሮቹ አንቀጽ ፴፱፣ ፵ ፣ ፵፩ ፣ ፵፪፣ እና ፵፫ አንቀጽ ፵፪ ፣ ፵፫፣፵፬ ፣ ፵፭ ፣ እና ፵፮ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡-

e) for trainings;

e) work for the media;

f) for business and market research;

g)for the entertainment industry; or

h) for a sports competition or practice."

4/ The following new Article 21 , 22 and Article 23 are added next to Article 20 of the Regulation, and the existing Articles from 21-41 are rearranged as to article 24-44:

"21. **<u>Medical visa</u>**

A medical visa is issued to a person who enters the country to provide or obtain medical care in a modern, cultural, or religious way and produces legal and valid travel documents.

22. **<u>Religious visa</u>**

A religious visa is issued to a person who has been invited or requested to enter the country for religious purposes only and submits a valid travel document.

23. **<u>Family or fiancé visa</u>**

A family or fiancé visa is issued to a person who is applying to visit family or meet his fiancé and submit a legal and valid travel document.”

5/ The following new part Eight and new Articles 39, 40 and 41 are added next to Article 38 of the Regulation (as renumbered in Sub-Article (4) of Article 2 of this Regulation) the existing part Eight become part nine and existing Article 39, 40, 41, 42, and 43 are re-arranged as Articles 42, 43, 44, 45, and 46:

" **ክፍል ስምንት**

**የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እና አስተዳደራዊ ቅጣት**

**፴፱. የፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ**

፩/ የፓስፖርት አገልግሎት እንዲሰጠው የሚፈልግ ተገልጋይ አገልግሎቱን ለማግኘት ባመለከተበት ቦታ ወይም ቅርንጫፍ መስርያ ቤት ብቻ አገልግሎቱን ማጠናቀቅ አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ የፓስፖርት አገልግሎት የሚፈልግ ተገልጋይ አገልግሎቱን ከጀመረበት ቦታ ወይም ቅርንጫፍ መስርያ ቤት ውጪ አገልግሎቱን ለማጠናቀቅ የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው አግባብ ካልተፈቀደ በስተቀር የአገልግሎቱ ሰራተኛ በሌላ ቅርንጫፍ የተጀመረን የፓስፖርት አገልግሎት እንዲጠናቀቅ ጥያቄ ሲቀርብለት አገልግሎት መስጠት የለበትም፡፡

፬/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው የተሰጠው ቪዛ ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በላይ በሀገር ውስጥ ለመቆየት ከፈለገ አገልግሎቱ ቪዛ እንዲሰጠው በድጋሚ መጠየቅ አለበት፡፡

**፵. አስተዳደራዊ ቅጣት**

፩/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው የፀና ቪዛ ሳይኖረው በሀገር ውስጥ የቆየ እንደሆነ ለቆየበት እያንዳንዱ ቀን ፴ የአሜሪካን ዶላር መክፈል አለበት፡፡ አገልግሎቱ እንደ አስፈላጊነቱ ድጋሚ ቪዛ ሊሰጠው ወይም ከሀገር ሊያስወጣው ይችላል፡፡

፪/ ከተፈቀደለት የቪዛ ጊዜ ውጪ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ የውጭ ሀገር ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተቀመጠው መቀጮ በተጨማሪ ሦስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ለቆየ ፫ሺ የአሜሪካን ዶላር ከፍሎ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

"**Part Eight**

**Passport Issuance and Administrative penalty**

**39. Issuance of passport**

1/ A customer who wishes to be issued a passport service must complete the service only at the place or branch where he applied for the service.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Director General of the Service may authorize for a customer seeking to complete a passport service outside of the place of commencement of the service or branch.

3/ Except as otherwise provided for in Sub-Article 2 of this Article, the employee of the Service shall not provide a service for a request of completion of a passport service initiated by another branch.

4/ Any foreign person who want to remain in the country beyond the valid date of the visa issued shall again request the Service for issuance of a visa.

**40. Administrative Penalty**

1/ Any foreign person who stays in the country without a visa shall pay 30 USD for each day he or she stays in the country without a visa; and the Service may re-issue a visa or deport him as may be necessary.

2/ A foreign person who stays in the country for a period not more than three years beyond the authorized visa period shall be deported after paying 3000 USD in addition to the fine set out in Sub-Article (1) of this Article.

፫/ ከተፈቀደለት የቪዛ ጊዜ ውጪ ከሦስት ዓመት በላይ ለቆየ የውጭ ሀገር ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተቀመጠው መቀጮ በተጨማሪ ፭ሺ የአሜሪካን ዶላር ከፍሎ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

፬/ በትራንዚት ቪዛ ወደ ሀገር የገባ የውጭ ሀገር ሰው ከተፈቀደለት የትራንዚት ቪዛ ጊዜ ውጭ በሀገር ውስጥ ከቆየ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተቀመጠው ቅጣት በተጨማሪ ፫ሺ የአሜሪካን ዶላር ከፍሎ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

፭/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተዘረዘሩትን የቅጣት ክፍያዎችን ለመሸፈን ፈቃደኛ ካልሆነና ንብረት ካለው በሕግ መሰረት በፍርድ ቤት ውሳኔ ንብረቱ ለወጪው መሸፈኛ ይውላል።

፮/ በሀገር ውስጥ የሚገኝ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያው ጊዜው ካለፈበት ከአስራ አንደኛው ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ካላሳደሰ ፻ የአሜሪካን ዶላር ተቀጥቶ መታወቅያው ይታደስለታል፡፡ ከአንድ ወር በላይ ከሆነ ላሳለፈበት ጊዜ በየወሩ በ፩፻፶ የአሜሪካን ዶላር እየተሰላ ቅጣት ከፍሎ መታወቅያው የሚታደስ ይሆናል፡፡

፯/ በውጭ ሀገር የሚኖር ትውልደ ኢትዮጵያዊ የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቅያው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካለፈ ፻ የአሜሪካን ዶላር ቅጣት በመክፈል ማሳደስ ይችላል፡፡

፰/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው የመኖሪያ ፍቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካለፈ በኋላ በሀገር ውስጥ የቆየ እንደሆነ ለቆየበት እያንዳንዱ ቀን ፴ የአሜሪካን ዶላር መክፈል አለበት፡፡ አገልግሎቱ እንደ አስፈላጊነቱ የመኖሪያ ፈቃዱን ሊያድስለት ወይም ከሀገር ሊያስወጣው ይችላል፡፡

3/ A foreigner who has stayed more than Three years beyond the authorized visa period shall pay a fine of 5000 USD in addition to the fines set forth in Sub Article (1) and (2) of this Article; and be deported from the country.

4/ A foreigner who entered the country with a transit visa and stays in the country beyond the granted transit visa period shall pay 3000 US dollars in addition to the fine set out in Sub Article (1) of this Article; and may be deported from the country.

5/ Any foreigner who is unwilling to pay the fines listed from Sub Article (1) up to (4) of this Article and has property, the property shall be used to cover the cost in accordance with the law.

6/ A foreign national of Ethiopian origin who is in the country and fails to renew his Ethiopian origin Identification Card within One month from the Eleventh day of its expiration date shall be fined 100 USD and renew his Identification Card. If he exceeds One month, he shall be fined 150 USD per month and renew his Identification Card.

7/ A foreign national of Ethiopian origin who is found abroad may renew his Ethiopian origin Identification Card by paying a fine of 100 USD if the validity period of his Identification Card has expired.

8/ Any foreigner who stays in the country beyond the validity period of his residence permit shall pay 30 USD for each day. The Service may renew his residence permit or deport him from the country as may be necessary.

፱/ የመኖሪያ ፈቃድ ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ ውጪ ከአንድ ዓመት በላይ የመኖሪያ ፈቃዱን ሳያሳድስ የቆየ የውጭ ሀገር ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ከተቀመጠው መቀጮ በተጨማሪ ፪ሺ የአሜሪካን ዶላር ከፍሎ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

፲/ ማንኛውም ከቪዛ ክፍያ ነፃ እንዲቆይ የተፈቀደለት የውጭ ሀገር ሰው ከተፈቀደው ጊዜ በላይ በሀገር ውስጥ ከቆየ ለቆየበት እያንዳንዱ ቀን ፲ የአሜሪካን ዶላር ተሰልቶ ቅጣት ይከፍላል፡፡

፲፩/ ከክፍያ ነጻ ቪዛ አግባብ ወደ ሀገር ገብቶ ከተፈቀደለት የቪዛ ጊዜ ውጪ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ የውጭ ሀገር ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) ከተቀመጠው መቀጮ በተጨማሪ ፩ሺ የአሜሪካን ዶላር ከፍሎ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

፲፪/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው ከተፈቀደለት ቪዛ አይነት ውጪ በሌላ ስራ ላይ ከተሰማራ የተፈቀደለት ቪዛ ተሰርዞ ፪ሺ ዶላር እና ሀገር ውስጥ ለቆየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፶ የአሜሪካን ዶላር እየተሰላ መቀጮ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ከሀገር እንዲወጣ እና ወደ ሀገር እንዳይገባ እግድ ሊተላለፍበት ይችላል፡፡

፲፫/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው ካስመጣው ድርጅት ወይም ግለሰብ ውጪ ለሌላ ድርጅት ወይም ግለሰብ አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተቀመጠው ቅጣት በተጨማሪ ፪ሺ ዶላር ይቀጣል። እንደ አስፈላጊነቱ ከሀገር እንዲወጣ እና ወደ ሀገር እንዳይገባ እግድ ሊተላለፍበት ይችላል፡፡

9/ A foreigner who has not renewed his residence permit for more than One year other than the validity period of his residence permit shall be deported after paying 2000 USD in addition to the fine set out in Sub-Article (6) of this Article.

10/ Any person who is allowed to remain exempt from visa fees for longer than the permitted period shall be fined 10 USD for each day he stays in the country.

11/ A foreigner who has entered the country for more than One year and has been outside the authorized visa period shall be deported after paying 1000 USD in addition to the fine set out in Sub-Article (8), of this Article.

12/ Any foreign person who engages in work other than the type of visa, authorized for him, his visa shall be revoked; and be fined 2,000 USD and 50 USD for each day he stays in the country. He may be deported or banned from entering the country as necessary.

13/ Any foreigner who is found providing services to another organization or individual other than the organization or individual that brought him, shall be fined 2000 dollars in addition to the fine set out in Sub Article1 of this Article. He may be deported or banned from re-entering the country as may be necessary.

፲፬/ ማንኛዉም የውጭ ሀገር ሰዉን ከተፈቀደለት ቪዛ አይነት ውጭ ሲያሠራ የተገኘ አሠሪ ለአንድ ዓመት በአገልግሎቱ ጥቁር መዝገብ የሚመዘገብ ሆኖ፡-

ሀ) የውጭ ሀገር ሰው ከሆነ ፲ሺ የአሜሪካን ዶላር እንዲከፍል ይደረጋል፤

ለ) ኢትዮጵያዊ ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተመለከተውን ቅጣት በወቅቱ ምንዛሪ በብር ተለውጦ ይከፍላል፡፡

፲፭/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጠውን ድንጋጌ በመተላለፍ ፓስፖርት ያገኘ ኢትዮጵያዊ በዚህ መንገድ ያገኘው ፓስፖርት የሚሰረዝ ይሆናል፤ ሆኖም ተገልጋዩ ከሁለት ዓመት በኋላ በህጋዊ መንገድ የጉዞ ሰነዱን እንዳያገኝ የሚከለክለው አይደለም፤

፲፮/ የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ህጋዊ የጉዞ ሰነድ ወይም ቪዛ ሳይኖረው በማንኛውም መንገድ ሀገር ውስጥ የተገኘ የውጪ አገር ሰው ፫ሺ የአሜሪካን ዶላር ከፍሎ ከሀገር እንዲወጣ ይደረጋል።

፲፯/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ እንደተገለጸው ያልፀና የጉዞና የይለፍ ሰነድ ሲገለገል የተገኘ ማንኛውም የውጭ ሀገር ሰው ሀገር ውስጥ ለቆየበት ለእያንዳንዱ ቀን እየተሰላ ፴ የአሜሪካን ዶላር መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ፫ሺ የአሜሪካን ዶላር መቀጮ ይከፍላል፤ አገልግሎቱ እንደአስፈላጊነቱ ከሀገር እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል፤

፲፰/ ማንኛውም የተጣለበትን የውጭ ሀገር ሰውን የማስመዝገብ ግዴታን ያልተወጣ ወይም ካስመዘገበው የውጪ ሀገር ሰው ጋር ግንኙነቱ ሲቋረጥ ያላሳወቀ ሰው፡-

ሀ) የውጭ ሀገር ሰው ከሆነ ፲ሺ የአሜሪካን ዶላር እንዲከፍል ይደረጋል፤

14/ Any employer who is found to be employing a foreigner out of a type of visa granted for him Shall be blacklisted by the Service for One year and:

a) If he is a foreign person, he shall pay 10,000 USD;

b) If he is an Ethiopian, he shall pay the penalty referred in letter (a) of this Sub-Article in exchange of the currency of the time.

15/ A passport which is obtained in violation of the provisions set forth in Sub-Article (1) of Article 39 of this Regulation shall be revoked; however, this does not prevent the customer from legally obtaining the passport after Two years as may be necessary;

16/ without prejudice to criminal liability, a foreigner found in the country by any means without a valid travel document or visa shall be fined with 3,000 USD and be deported.

17/ A person found using an invalid travel document or visa shall pay 3000 US dollars in addition to a fine set forth on Sub Article (1) of this Article; and the Service may deport him as may be necessary;

18/ Any person who does not comply with the obligation to register a foreigner or who does not notify when the relationship with the registered foreigner is terminated:

a) If he is a foreigner, he shall pay 10,000 USD;

ለ) ኢትዮጵያዊ ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተመለከተውን ቅጣት በወቅቱ ምንዛሪ በብር ተለውጦ ይከፍላል፡፡

፲፱/ ማንኛውም የህግ ሰውነት ያለው ሰው በህግ በተጣለበት ኃላፊነት መሠረት ህጋዊ ተወካዩን ያላስመዘገበ እና የተወካይ ለውጥ ሲኖርም ለአገልግሎቱ ያላሳወቀ እንደሆነ፡-

ሀ) የውጭ ሀገር ሰው ከሆነ ፭ሺ የአሜሪካን ዶላር እንዲከፍል ይደረጋል፤

ለ) ኢትዮጵያዊ ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ላይ የተመለከተውን ቅጣት በወቅቱ ምንዛሪ በብር ተለውጦ ይከፍላል፡፡

፳/ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን አስተዳደራዊ ቅጣት ከተቀጣ በኋላ ሌላ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስቀጣ ጥፋት የፈጸመ ሰው ለየጥፋቱ የተቀመጠውን ቅጣት ሁለት እጥፍ መቀጮ እንዲከፍል እና እንደነገሩ ሁኔታ ከሀገር እንዲወጣ ወይም ወደ ሀገር እንዳይገባ ሊታገድ ይችላል::

፳፩/ በዚህ አንቀጽ የተቀመጡት የቅጣት ክፍያዎች በአሜሪካን ዶላር መከፈላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቀጭው ቅጣቱን በአውሮፓ ህብረት የጋራ መገበያያ ዩሮ ወይም በእንግሊዝ ፓውንድ በአማራጭነት መክፈል ይችላል፡፡

**፴፱. ልዩ ሁኔታ**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፵ ላይ የተጠቀሰውን መቀጮ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መክፈል የማይችሉ ወይም መክፍል የሌለባቸዉ ሰዎችን በተመለከተ በአገልግሎቱ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡”

b) If he is an Ethiopian, he shall pay a fine mentioned in Paragraph (a) of this Sub Article by changing in to Birr based on the current currency.

19/ Any juridical person who did not register his legal representative in accordance with the responsibility imposed by law or did not inform the service if there is a change of representative :

a) If he is a foreigner, he shall pay 5000 US dollars;

b) If he is an Ethiopian, he shall pay the fine mentioned in Paragraph (a) of this sub Article by changing in to Birr based on the current currency.

20/ A person who commits again another offense punishable by administrative penalty after an administrative penalty stipulated in this Article, shall be fined double of the penalty set for the offenses respectively; and may be deported or banned from entering the country as the case may be.

21/ Without prejudice to the penalty fees outlined in this article be paid in US dollars, the penalty may be paid in the common currency of the European Union in euros or the British pound alternatively.

**39. Exception**

Regarding persons who are unable or unwilling to pay the fine mentioned in Article 40 of this Regulation, up on force majeure, shall be determined by the Directive issued by the Service."

፮/ የደንቡ አንቀጽ ፵፫ (በዚህ ደንብ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፭) ላይ እንደተሸጋሸገ) ተሰርዞ ነባሮቹ አንቀጾች ፵፬፣፵፭፣ እና ፵፮ አንቀጽ ፵፫፣ ፵፬፣ እና ፵፭ ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

፯/ የደንቡ አንቀጽ ፵፬ (እንደተሸጋሸገ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፬ ተተክቷል።

“፵፬. <u>**የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**</u>

፩/ በደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀፅ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ) እና (ሐ) ላይ ፓስፖርት ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በተመለከተ የተሻሻለው የፓስፖርት ጸንቶ የመቆያ ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነዉ ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሁለት አመት ዉስጥ ይሆናል።

፪/ አገልግሎቱ በደንቡ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣(ለ) እና (ሐ) መሰረት ፓስፖርት እስኪሰጥ ድረስ የተሰጠ ፓስፖርት ጸንቶ መቆያ ግዜ በፓስፖርቱ ላይ የተገለጸዉ ጸንቶ መቆያ ጊዜ ይሆናል፡፡”

፫. <u>**ደንቡ የሚጸናበት ግዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ።**

**ዶ/ር አብይ አህመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚንስትር**

6/ Article 43 of the Regulation (as rearranged by Sub-Article (5) of Article 2 of this Regulation) is deleted and the existing articles 44, 45, and 46 are rearranged as Article 43, 44, and 45.

7/ Article 44 of the Regulation (as rearranged) is .deleted and replaced by the following new Article 44.

“**44. <u>Transitory Provisions</u>**

1/ The amended validity period of a passport stated on paragraphs (a), (b) and (c) of Sub-Article (1) of Article 11 of the Regulation shall come into force within Two years from the effective date of this Regulation.

2/ Until the service issues new validity period of passport in accordance with Paragraphs (a), (b) and (c) of Sub-Article (1) of Article 11 of the Regulation the validity period of a passport shall be the period specified on the passport. ”

**3. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall be effective from the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of October 2024.**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**